ቀስተደመና ሬድዮ 31/03/00

# አንበትነው:: እንቋጥረው

መጭውን የግንቦት ምርጫ አስመልክቶ የኢተፖድሀ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ባለፈው መስከረም ወር በፍራንክፈርት ከተማ 'ለምርጫው እንቅስቃሴ ተመዝገቡ' ብሎ ያስተላለፈው ውሳኔ ቀጣይነት ላለው ትግል መነሳሳት ለቆሙ ኃይሎች ሁሉ ምን ያህል ትክክለኛ ስትራቴጂ እንደሆነ ዛሬ በግልጸ እየታየ ነው:: የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ በወያኔ የምርጫ ግርግር በመሳተፍ ለአንዳንድ ተቃዋሚያች ምንም የማይፈይዱበት የወያኔ ፖርላሜንት ውስጥ የተወሰነ መቀመጫ ለማስገኘት አልነበረም:: ዋና ዓላማው እስከ ግንቦት ድረስ በምርጫው ጥያቄ ዙሪያ ህዝባችንን ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስና ይህ የሚነሳሳው ህዝባዊ ትግል ደግሞ ከግንቦቱ ግርግር በኋላ ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲሆን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር::

በአሁኑ ወቅት በዚህ ምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ በሃገራችን በአንድ በኩል በወያኔ ካድሬያች በሌላ በኩል ደግሞ በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ለመመዝገብ በሞከሩና ለዚህም ድጋፍ በሰጡቸው ዜጎች መሃከል ከፍተኛ የአፈናና የትግል አዙሪት ውስጥ ገብተን እንገኛለን:: የወያኔ ካድሬያች የአፈና፣ የግድያ፣ የቤትና ንብረት ማቃጠል፣ ከመሬት የመንቀልና ከሥራ የማፈናቀል ውርጅብኝ ሳይገታቸው በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎች ለውድድር ተመዝግበዋል:: ሚልዮን የማያንሱ ሌሎች ዜጎች ደግሞ የድጋፍ ፊርማ ሰጥተዋል::ይህ እጅግ ከፍተኛ ድፍረትና የትግል ወኔን የሚጠይቅ የፖለቲካ ርምጃ እንኳ እንደወያኔ ዓይነት አፋኝ አገዛዝ በሰፈነበት አገር ለንደን ወይም ዋሽንግተን አውራ ጎዳናያች ላይ እንደሚፈረም ፒቲሽን ሆኖ የሚታይ ቀላል ነገር አይደለም::

በአጭሩ ዛሬ በሃገራችን ምናልባት ከአንድ ትውልድ ወዲህ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ለለትግል ያመቸ ሁኔታ አለ:: ጥያቄው ምርጫው ውስጥ የመሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ጥያቄ አይደለም:: ይህንን ትግል እንዴት እናስተባብረው? ኢሉባቦር ያለውን ታጋይ ጎንደር ከወያኔ ካድሬ ጋር ከተፋጠጠው ፣ አዲስ አበባ የሚንቀሳቀሰውን ኃይል ሐረር ከወያኔ ካድሬ ጋር ከሚዋደቀው ተቃዋሚ ጋር እንዴት አገናኝተን ይህንን ትግል ከግንቦት ባሻገር ቀጣይነት እንዲኖረው እናስተባብረው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ለዚህ መልስ ለመስጠት ደግሞ የሚመጡት ወራት ወሳኝ ወራት ናቸው:: ተቃዋሚ ኃይሎች እንዲህ ዓይነቱን ሞመንተም /እመርታ/ ተባብረው የተባበረ አመራር ~~[illegible]~~ መስጠትን ትተው እንደገና " በቀጣዩ የ1997 ዓ.ም. ምርጫ በተመሳሳይ ፕሮግራም እስክንገናኝ...." ብለው ሊያሰናብቱት ከሞከሩ ይህ እመርታ/ ሞመንተም/ ለረዥም ጊዜ መልሶ ለማንሰራራት ምንም ተስፋ በሌለው ሁኔታ ከስሞ ይቀራል::

ካወቅንበት ደግሞ አሁን አምቦ ሆነ ወላይታ፣ ባህር ዳር ሆነ ሃድያ፣ በረና ሆነ አዲስ አበባ የሚካሄደው ትግል መነሻው አንድ የወያኔ ጸረ ህዝብ አገዛዝ፣ መፍትሄውም ይህንን ኃይል በሰላማዊና በጋራ የፖለቲካ ትግል መጋፈጥ መሆኑን ተገንዝበን ሰማይ ወጥተን ምድር ገብተን በአጣዳፊ እናስተባብረዋለን:: ይህንን ትግል መቋጠርና መልክ ማስያዝ ካላወቅንበት ግን በእንዲህ ዓይነት አመቺ ሁኔታ ለመጠቀም ያልቻልን ሃይሎች መቼና እንዴት ተንቀሳቅሰን ይህንን ሊበተንና በተስፋ መቁረጥና ውዠንብር ባህር ውስጥ መልሶ ሊዘፈቅ የሚችል የህዝብ ትግል ልንቀሰቅሰው እንደምንችል ለማንም ግልጸ አይደለም::

በጋራ ትግል ህዝቡን የማስተባበሪያውና ከያለበት በመቀጣጠል ላይ ያለውን ትግል
የመቋጠሪያው ጊዜው ዛሬ ነው፡፡ በተደጋጋሚ የታሪክ አጋጣሚ ያመለጣቸው የኢትዮጵያ ዴሞ
ክራቶች ዛሬ ይህንን ሃላፊነት መቀበል ካቃታቸው ነገ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ስለትግል፣ ስ
ስለዴሞክራሲ፣ ስለፍትህ፣ ስለጸረ ወያኔነት ደፍረው መናገር የሚችሉበት ሁኔታ እጅግ እ
ንደሚጠብ ከወዲሁ መገንዘብ አለባቸው፡፡ ባጭሩ ይህንን ትግል አንበትነው፣ እንቋጥረው
የሚለው መፈክር ወቅታዊ አንገብጋቢ ነው፡፡

ቀስተደመና ሬድዮ
31/03/00